# ማ ሳ ስ ቢ ያ

በዚህ መፍሐፍ ውስጥ የሚገኙት ስታትስቲካዊ መረጃዎች በ1989 የነበረውን የመሠረተ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን የአጥቢያ ቤተክርስቲያናት የምዕመናን የስርጭትና የክልሎችን ብዛት የሚያሳይ ነው። በአሁኑ ማለትም በነሐሴ 1992 ዓ.ም. ያለው መረጃ ግን እንደሚከተለው ነው። በ1998 ዓ.ም. ነሐሴ ወር ያለው መረጃ ተካቷል።

| | 1992ዓ.ም. | 1998 ዓ.ም. |
|---|---|---|
| 1.ጠቅላላ የምዕመናን ቁጥር | 167.067 | 294.491 |
| 2.የአባላት ቁጥር /የተጠመቁ/ | 112.009 | 144.787 |
| 3.ያልተጠመቁ /በክትትል ላይ ያሉ/ | 451.566 | 451.566 |
| 4 የልጆች ቁጥር | 55.68 | 104.491 |
| 5. የአጥቢያ ቤተክርስቲያናት ብዛት | 248 | 398 |
| 6. የስርጭት ጣቢያዎች ብዛት | 604 | 789 |
| 7. የክልሎች ብዛት | 16 | 19 |
| 8.የሙሉ ጊዜ አገልጋዮች ብዛት | | 1.931 |


**የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ባፕቲስት ቤተክርስቲያን**

**Ethiopian Evangelical Baptist Church**

2822 S. Jupiter Rd.
Garland, TX 75041
Tel: (214) 703-0100 Fax: (214) 703-0161
WWW.EEBC-DALLAS.ORG

## ስለ ፀሐፊው

ይህን ጽሑፍ የጻፉት አቶ በድሩ ሁሴን ከ 1983-1989 በመሰረተ ክርስቶስ ቤቴክርስቲያን ዋናው ቢሮ በተ/ዋና ፀሀፊነት በኋላም በዋና ፀሐፊነት አግልግለዋል። ክርስቲያን የሆኑት በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተማሪ በነበሩበት ጊዜ ነበር።

በመሰረተ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን በሙሉ ጊዜ አገልጋይነት ከመሥራታቸው በፊት በመንግስትና ቤተክርስቲያን ሁለትኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በመምህርነት ከዚያም በብሄራዊ ጤና ምርምር ኢንስቲቲዩት አገልግለዋል። በነዚህ ዘመናት በቤተክርስቲያን ውስጥ አገልግሎታቸው የጎላ ተሳትፎ አድርገዋል። ከ1990 ዓ.ም ጀምሮ የስነመለኮት ትምህር ለማር ተልከው በማስተርስ ደረጃ ማስተር ኦፍ ዲቪንቲ አግኝተው ተመልሰዋል በ1993 ዓ.ም ጀምሮ በመሰረተ ክርስቶስ ኮሌጅ በተለያየ ሀላፊነቶችና በመምህርነት በማገልገል ላይ ይገኛሉ አቶ በድሩ ሁሴን ባለትዳርና የአራት ልጆችና እንዲሁም የ 5 የልጅ ልጆች ባለጸጋ ናቸው። በህይወት ዘመናቸው የሚወዱትና የሚጠቀሱት 26/27/4 ነው እግዚአብሔርን አገልግለው ማለፍ ለተተኪ መሪዎች የሚያግዙ ጽሁፎችን ትተው ወደዘላለም ቤታቸው መሄድ ያስባሉ።



## ይህ መጽሐፍ ስለምን አስፈለገ?

አንድ ቀን ስለመሠረተ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን በጥልቀት ለመረዳት ከፈለገ ሰው ጋር በቢሮዬ እነጋገር ነበር። በተለይ መሠረተ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ከሌሎች ቤተክርስቲያናት ይልቅ በገንዘብ በኩል የተሻለ እራሷን ልታስተዳድር የሚቻልበትን መንገድ እንዴት እንዳገኘች ለማወቅ የፈለገ ሰው ነበር።

መልሴ በጣም ቀላል ነበር። ይኸውም ባለአደራነት፣ የቤተክርስቲያን አመራር ለተጠያቂነትና ለግልጽነት የተመቻቸ ሁኔታ መኖራቸው እንደሆነ ባጭሩ ገለጽኩለት።

ይህም ባጭሩ

1. ለእግዚአብሔር ሥራ ገንዘብን መስጠትና ይህን ለማረጋገጥና ስለባለአደራነት የማያቋርጥ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት መስጠት
2. የበሰሉ ክርስቲያን መሪዎችን ለማፍራት ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ
3. የተጠያቂነትና የግልጽነትን መርህ በማመንና በተግባር ለምዕመኑ በማሳየት ናቸው።

ቤተክርስቲያን እነዚህን ሦሥት መሠረታዊ ነገሮች በቁርጠኛነት በተግባር ላይ ካዋለችና ከተለማመደች ከጥገኛነት ወደ እውነተኛ ራሷን ወደ መቻል ደረጃ ትደርሳለች። ቤተክርስቲያን በእውነት ራሷን መደገፍ ከቻለች በሌላው ዓለም ከሚገኙት ሌሎች ቤተክርስቲያናት ጋር በእውነተኛ መንፈስ የመደጋገፍና የመተባበር አቋም ላይ ትደርሳለች።

እነዚህን ጉዳዮች ነው በዚህች አነስተኛ ጽሑፍ ውስጥ ከዚህ በኋላ የምንመለከተው።



# ክፍል አንድ

## ሀ. ባለአደራነት ምን ማለት ነው?

አንተ እንድትበልጥ ማን አድርጎሃል?
ያልተቀበልኸውስ ምን አለህ? የተቀበልህ
ከሆንህ ግን እንዳልተቀበልህ የምትመካ ስለምንድነው?
( 1ቆሮ. 4:7)

ባለአደራነትን በሚገባ ለመረዳት እግዚአብሔር በቃሉ የሚለንን ማወቅ ይኖርብናል። ነገሩን ለመረዳት እርሱ ስለዚህ ጉዳይ በሚጀምርበት ሥፍራ መጀመር አለብን። ይኸውም ባለአደራነት ራሱ በእግዚአብሔር ባሕሪ ላይ መሠረት ያደረገ ጉዳይ መሆኑን ማወቅ አለብን። ይህ ከሆነ ደግሞ ባለአደራነት በሰው ባሕሪም ላይ መሠረት ያለው እንደሆነ ልንገነዘብ ያስፈልጋል።

### 1. እግዚአብሔር የሁሉ ነገር ፈጣሪ ነው

ጌታችንና — አምላካችን ሆይ አንተ
ሁሉን — ፈጥረሃልና ስለፈቃድህም
ሆነዋልና — ተፈጥረዋልምና ክብር
ውዳሴ — ኃይልም ልትቀበል ይገባሃል። (ራዕይ 4:11)

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር በመጀመሪያ ሰማይንና ምድርን እንደፈጠረ ያስተምራል። (ዘፍ. 1:1) ይህ በጣም አስደናቂ የሆነው የእግዚአብሔር ቃል መክፈቻ ዐረፍተነገር እግዚአብሔር የሁሉ ነገር ምንጭ እንደሆነ ይገልጻል። አዲስ ኪዳንም ይህን እውነት የሆነውን መሪ ሃሳብ የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ የሁሉ ነገር ፈጣሪ እንደሆነ ወይም ፍጥረት ሁሉ ባእርሱ እንደተፈጠረ ያመለክታል። ይኸውም "ሁሉ በእርሱ ሆነ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለእርሱ አልሆነም" በማለት ያበሥራል።(ዮሐ.1:3)

ይህ "ፍጥረት" በሚለው ቃል ማንኛውንም ነገር ሲያጠቃልል ሰውንም ይጨምራል።

## 2. እግዚአብሔር የሁሉ ነገር ባለቤት ነው

እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ስለፈጠረ የሁሉም ነገር (የተፈጠረው ነገር) ሁሉ ባለቤት ነው ማለት ይቻላል። እርሱም በቃሉ "ምድር ሁሉ የእኔ ናትና" (ዘፀ. 19:5) በማለት ያረጋግጣል። እንግዲህ በዚህ በጣም ቀላል በሆነ እውነት ላይ ነው ባለአደራነት የተመሠረተው። ወይም መነሻነት ያገኘው።

በምድር ላይ በአመዛኙ ባለቤትነት የምንለው ነገር በሕግ ላይ የተመሠረተ ነው። አንድ ሰው ለምሳሌ መሬት ወይም ቤት ቢኖረው



ባለቤት ለመሆኑ የባለቤትነት ሕጋዊ መረጃ ያስፈልገዋል። በመጽሐፍ ቅዱሳዊ አመለካከት ግን ማንኛውም ባለቤትነት (ሐብት፣ ጊዜ፣ እኛ ራሳችን) ወደ ምንጩ ወደ ኋላ ብንሄድ የእግዚአብሔር እንደሆንን እንረዳለን። እንደመጽሐፍ ቅዱስ አገላለጽ የእግዚአብሔር ባለቤትነት ፍጽምነት ያለው ነው። ወይም ባጭሩ እግዚአብሔር የሁሉ ነገር ባለቤት ነው።

ምድርና መላዋ ለእግዚአብሔር ናት
ዓለምም በእርስዋም የሚኖሩ ሁሉ
እራሱ በባሕሮች መሥርቶታልና
በፈሳሾችም አጽንቷታልና (መዝ. 23(24) : 1 - 2)

የምድረበዳ አራዊት ሁሉ
በሺ ተራራዎች ያሉ እንስሶችም የእኔ ናቸው።
የሰማይን አዕዋፍ ሁሉ አውቃለሁ
የምድረበዳ አራዊትም በእኔ ዘንድ ናቸው።
ብራብም ለአንተ አልነግርህም፤
ዓለምና ሞላዋ የእኔ ነው·ና። (መዝ. 49(50) : 10 -12)

ብሩ የእኔ ነው፣ ወርቁም የእኔ ነው
ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር (ሐጌ 2:8)

በእግዚአብሔር ተፈጥረው ባለአደራነት ተሰጥቷቸው ሳለ ግንኙነታቸው በኃጢያት ምክንያት እንደተቋረጠ ያመለክተናል።

እግዚአብሔር በመጀመሪያ ከፈጠራቸው በኋላ በጣም ውብ በሆነ የመኖሪያ አካባቢ አስቀመጣቸው። በዚሁም ሥፍራ ሆነው ከእግዚአብሔር ጋር ፍጹም ሕብረትና አንድነት ሲኖራቸው የተመቻቸ ሁኔታ ላይ ነበሩ። እግዚአብሔር ለነዚህ ሰዎች በፈጠራቸው ነገሮች ላይ የባለአደራነት ሃላፊነት ሰጣቸው። ከዚህም ጋር መጠበቅ ብቻ ሳይሆን መንከባከብም ተጨማሪ ሃላፊነታቸው ነበር። ነገር ግን ሰይጣን ወደዚህ ሥፍራ መጥቶ "በእውቀትና" "ኃይል" ፈተናቸው አላቸውም:- "እንደ እግዚአብሔር ትሆናላችሁ" (ዘፍጥረት 3:5) እነርሱም አመኑት። የእግዚአብሔርንም ትዕዛዝ ጣሱ።

አለመታዘዝ ኃጢያት ነው። ይህም ኃጢያት ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸውን ፍጹም ግንኙነትና ሕብረት እንዲቋረጥ አደረገ። ከዚህ የተነሳ እግዚአብሔር ከፈጠረው ሰው ጋር ተለያየ። ይህ ነበር የሰው ውድቀት መነሻ ምክንያት። ይህም በሰው ታሪክ ውስጥ ከእግዚአብሔር መለየትን ያስከተለው።

> "ስለዚህ ምክንያት ኃጢያት በአንድ ሰው ወደዓለም ገባ። በሐጢዓትም ሞት እንደዚሁም ሁሉ ኃጢአትን ስላደረጉ ሞት ለሰው ሁሉ ደረሰ።" (ሮሜ 5:12)



አዳምና ሔዋን ከእግዚአብሔር አምላክ ጋር የነበራቸውን ግንኙነት አቋረጡ። ከዚያን ጊዜ ጅምር ሰው በእግዚአብሔር ላይ የመደገፉን፣ የመታመኑንና የተጠያቂነቱን ሚና ረሳ። በተፈጥሮ በራሱ የሚታመንና ነፃ እንደሆነ በመቁጠሩ ያለው ነገር ሁሉ እግዚአብሔር የፈጠረው ዓለምና ራሱም ጭምር የራሱ እንደሆነ መቁጠር ጀመረ።

## 5. ደህንነትና ባለአደራነት

ከውድቀት በኋላ እግዚአብሔር ሰውን እንዲሁ ሊተወውና ሊረሳው ይችል ነበር። ሰው እምነት በማጉደሉ መልሶ ወደነበረበት ደረጃ ለማውጣት እግዚአብሔር ግዴታ አልነበረበትም። በመተውም ጻድቅነቱንና ቅድስናውን የሚያጣ አምላክ አልነበረም። ነገር ግን እራሱ ለሰው ልጆች ምህረቱን አሳየ። መሃሪነቱን ገለጸ።

እንዲያውም ሰው በእግዚአብሔር ላይ ባመፀበትና ግንኙነትና ሕብረት ባቋረጠበት ሁኔታ እግዚአብሔር አዳኝ እንደሚልክ ቃል ገባ (ዘፍ. 3:15) ቃሉንም ጠብቆ ሰዓቱ በደረሰ ጊዜ እየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም በመምጣት ለሰዎች ሁሉ ሞትን ሞተ (ቲቶ 2:14)። ከዚህ የምንረዳው በመጀመሪያ ሰው በእግዚአብሔር በመፈጠሩ ባለቤቱ እግዚአብሔር መሆኑን፣ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ክርስቶስ ለእርሱ በመሞቱ በደሙ ሰውን መግዛቱን (መዋጀቱን) ነው። ስለሆነም ሰው ወደ አዲስ ግንኙነት ተሸጋግሯል። የክርስቶስ ሞት እኛን ሁለት

ይህ ታሪክ ከመጽሐፍ ቅዱስ አይደለም። ሆኖም ምሳሌ ሆኖ ሊያገለግለን ይችላል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ባለአደራዎች (ሃላፊነት ስለተሰጣቸው) ብዙ ምሳሌዎች ተናግሯል። ሁሉም የሚያመለክቱት ታድያ ያለን ሁሉ የእርሱ መሆኑን ነው።

"ወደ ሌላ አገር የሚሄድ ሰው ባሮቹን ጠርቶ ያለውን ገንዘብ እንደ ሰጣቸው እንዲሁ ይሆናልና። ለእያንዳንዱ እንደ አቅሙ ለአንዱ አምስት መክሊት ለአንዱ ሁለት ለአንዱም አንድ ሰጠና ወደ ሌላ አገር ወዲያው ሄደ። አምስት መክሊትም የተቀበለው ሄዶ ነገደበት ሌላም አምስት አተረፈ። እንዲሁም ሁለት የተቀበለው ሌላ ሁለት አተረፈ። አንድ የተቀቀበለው ግን ሄዶ ምድርን ቆፈረና የጌታውን ገንዘብ ቀበረ። ከብዙ ዘመንም በኋላ የእነዚያ ባሮች ጌታ መጣና ተቆጣጠራቸው። አምስት መክሊት የተቀበለውም ቀረበና ሌላ አምስት መክሊት ሰጥተኸኝ ነበር እነሆ ሌላ አምስት መክሊት አተረፍሁበት አለ። ጌታውም መልካም አንተ በጎ ታማኝም ባሪያ በጥቂቱ ታመነሃል በብዙ እሾምሃለሁ ወደ ጌታህ ደስታ ግባ አለው። ሁለት መክሊትም የተቀበለው ደግሞ ቀርቦ ጌታ ሆይ ሁለት መክሊት ሰጥተኸኝ ነበር እነሆ ሌላ ሁለት መክሊት አተረፍሁበት አለ። መልካም አንተ በጎ ታማኝም ባሪያ በጥቂቱ ታምነሃል በብዙ እሾምሃለሁ ወደ ጌታህ ደስታ ግባ አለው። አንድ መክሊትም የተቀበለው ደግሞ ቀርቦ ጌታ ሆይ ካልዘራህባት የምታጭድ ካልበተንህባትም የምትሰበስብ ጨካኝ ሰው መሆንህን አውቃለሁ። ፈራሁም ሄጄም



መክሊትህን በምድር ቀበርሁት። እነሆ መክሊትህ አለ። ጌታውም መልሶ እንዲህ አለው። አንተ ክፉና ሃኬተኛ ባሪያ ካልዘራሁባት እንዳጭድ ካልበተንሁባትም እንድሰበስብ ታውቃለህን? ስለዚህ ገንዘቤን ለለዋጮች አደራ ልትሰጠው በተገባህ ነበር። እኔም መጥቼ ያለኝን ከትርፉ ጋር እወስደው ነበር። ስለዚህ መክሊቱን ውሰዱበት አሥር መክሊትም ላለው ስጡት። ላለው ሁሉ ይሰጠዋልና። ይበዛለትማል። ከሌለው ግን ያው ያለው እንኳ ይወሰድበታል። የማይጠቅመውንም ባሪያ በውጭ ወዳለው ጨለማ አውጡት በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል።" (ማቴ. 25:14 - 30)

## ባጭሩ ታዲያ "ባለአደራ" ማን ነው?

ሁሉም ነገር የእግዚአብሔር ነው። በእግዚአብሔር በሆነ ነገር ሁሉ ላይ ክርስቲያኖች አስተዳዳሪዎች እንዲሆኑ ሃላፊነት ተሰጥቶአቸዋል። በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ሃላፊነት ለመረከብ መቻልና መታመን ማለት የባለአደራነት ሥራን መስጠት ማለት ነው። ለምሳሌ:- "የኔ ቤተክርስቲያን" ብዙ ጊዜ እንላለን። ይህ ከባለአደራነት አኳያ ትክክል አይደለም። "የማገለግላት ቤተክርስቲያን" ብንል ግን ባለቤቱ ማን እንደሆነና አገልጋዩ ደግሞ ማን እንደሆነ ማወቅ እንችላለን።

## ሊ. የመልካም ባለአደራ ምልክቶች ምንድናቸው?

1. <u>ትህትና</u>:- የምናገለግለው ከትዕቢት ወይም ስለማንነታችን ወይም ካለብን የሃላፊነት ሥፍራ ወይም ከዚህ በፊት ካከናወናቸው መልካም ሥራዎች የተነሣ መሆን የለበትም። የምናገለግለው በክርስቶስ ማን መሆናችን በመረዳታችን መሆን አለበት። ለእርሱ የምንሰጠው ምላሽ ከመልካም ባለአደራ ከሚጠበቅ የትህትና ሕይወት የመነጨ መሆን ይኖርበታል (ፊሊ. 2: 3 - 16)
2. <u>ዕውቀትና ጥበብ</u>:- እግዚአብሔርን ማወቅ ማለት እርሱ ኃያል እንደሆነና መታዘዝን የሚፈልግ አምላክ መሆኑን መረዳት ማለት ነው። ከዚህ አመለካከት (እውነት) በመነጨ ሁኔታ ውስጥ ነው ሰው እግዚአብሔር በሰጠው ሃላፊነት በቤተክርስቲያን ውስጥ በጥበብ ማገልገል የሚችለው (ምሳሌ 1:7፤ ሆሴዕ 4:1,6፤ ምሳ. 8)
3. <u>መረዳት (ማስተዋል)</u>:- የክርስቲያን ባለአደራነት ምን ማለት እንደሆነ መረዳት ያስፈልገናል። የዚህ መጽሐፍ ክፍል አንድ በሙሉ ይህን በተመለከተ የሚያጠቃልል ስለሆነ መረዳት ይኖርብናል።
4. <u>ታማኝነት</u>:- አንድ አገልጋይ ራሱን ለተሰጠው ሃላፊነት (ባለአደራነት) በታማኝነት በቅንነት በታዛዥነትና



በንጽህና አገልግሎት መስጠት ይጠበቅበታል (የሐዋ.24፤16, 2ቆሮ. 4፤1,2, ቲቶ 1፤7 , ምሳሌ 11.3, ቲቶ 3፤1)

5. <u>ከራስ ወዳድነት የተላቀቀ ሕይወት</u>:- የራሳችንን ጥቅም በመተው ስለሌሎች ሰዎች ደህንነትና ብልጽግና በማሰብ ልናገለግል ይገባናል። (2ቆሮ. 9:12 - 14)

# ክፍል ሁለት (ሀ)

## አሥራት:- ከቤተክርስቲያን ባለአደራነት አንዱ ክፍል ነውን?

በቤቱ ውስጥ መብል እንዲሆን
አሥራቱን ሁሉ ወደጎተራ አግቡ
የሰማይንም መስኮት ባልከፍትላችሁ
በረከትንም አትረፍርፌ ባላፈስላችሁ
በዚህ ፈትኑኝ ይላል የሠራዊት
ጌታ እግዚአብሔር። (ሚልኪያስ 3:10)

ብሉይ ኪዳንም ሆነ አዲስ ኪዳን ለእግዚአብሔር ስለሰጠን በረከት መልሰን በገንዘብ ሆነ በዓይነት መስጠት እንዳለብን ይጠቅሳሉ። በዕብራይስጥ ቃል አሥራት (ማአሰር Maser) ነው። ይህም ቀጥተኛ (የፊት ለፊት) ትርጉሙ ከአሥር አንድ ማለት ነው።

### ሀ. አሥራት:- በብሉይ ኪዳን አመለካከት

1. በብሉይ ኪዳን በእግዚአብሔር ሕግ መሠረት እሥራኤላውያን አንድ አሥረኛ (1/10) ከከብትና ከመሬት ከሚያገኙት ሁሉ መሥጠት እንደነበረባቸው ያመለክታል። (ዘሌዋውያን 27:30 - 32 ፤ ዘሑልቁ 18:21, 26) የገባው አሥራት የሚውለው ለአምልኮ ሥርአት ለሰዎችና ለካህናቱ የኑሮ መደገፊያ ነበር። የምድርም አሥራት ወይም በምድር ዘር ወይም የዛፍ ፍሬ ቢሆን የእግዚአብሔር ነው። ለእግዚአብሔር የተቀደሰ ነው። (ዘኁልቁ 27:30)
2. ከአሥራቱም በተጨማሪ እሥራኤላውያን ለእግዚአብሔር የተለያዩ ሥጦታዎችን እንዲያቀርቡ ተጠይቀዋል። በአመዛኙ ለመስዋት የሚሆኑ ነገሮች ነበሩ። የዘለዋውያን መጽሐፍ ይህን በተመለከተ ከነአቀራረብ ሥርአቱ በዝርዝር ያቀርባቸዋል። ይኸውም የግል መስዋዕት፣ የሕብረት መሥዋዕት፣ የደህንነት መስዋዕት በማለት ይዘረዝራቸዋል (ዘሌዋውያን 6, 7: 1 - 10) እሥራኤላውያን በተጨማሪም በፈቃደኝነት ለጌታ የሚያቀርቡት መስዋዕት ነበራቸው። ሐዋ. 22:11 - 23, ዘዳግም 12:6, 11)
3. በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ስለአሥራት ሕግ (ትዕዛዝ) የሰጠበት ዋና ምክንያቱ እርሱ የሁሉ ነገር ባለቤት እንደሆነም ለማመልከት ነበር። (ዘጸአት 19:5, መዝ. 23(24) :1, 50,10 - 12, ሐጌ 2:8)

ምድርና መላዋ ለእግዚአብሔር ናት
ዓለምም በእርስዋም የሚኖሩ ሁሉ
መዝ. 23(24)፤1

ብሉይ ኪዳን ስለአሥራትና መባ (ሥጦታ) የተጠቀሱት ምሳሌዎች ሁሉ ስለገንዘብና ስለ ማቴሪያል ለባለአደራነት መሠረታዊ የሆኑ መርሆች በአዲስ ኪዳንም እውነትነት አላቸው።

## ለ. አሥራት:- በአዲስ ኪዳን አመለካከት

በአዲስ ኪዳን በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሁለት ጊዜ ስለአሥራት ተጠቅሷል። ሉቃስ 11፤42 እንዲሁም። (በሉቃስ 18:12) በእነዚህ ሁለት ክፍሎች ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሊያሳይ የፈለገው ከአሥራት መስጠት ሕግ ይልቅ የመስጠቱን መንፈስ ነበር።

ሐዋርያው ጳውሎስ "አሥራት" የሚለውን ቃል አይጠራም። ሆኖም ጌታ እንዳበለጸገን መስጠት እንዳለብን ያስተምራል። መስጠቱ በተለይ በቋሚነት ሥርዓትን በተከተለና በለጋስነት መሆን እንዳለበት አበክሮ ይመክራል።

የመስጠትን ጉዳይ በተመለከተ ኢየሱስም ሆነ ጳውሎስ ያስመሩበት ነገር ነው። ጳውሎስ እንዴት መስጠት እንዳለበት ሲጠቅስ ጌታ ኢየሱስ ደግሞ የምንሰጥበትን መንፈስ ይናገራል። ሁለቱም ቢሆኑ ከብሉይ ኪዳን ያነሠ ወይም ዝቅ ያለ መስጠት እንዳለብን አያመለክቱም። መስጠት ሕግን የተመረኮዘ መሆን አይኖርበትም። ነገር ግን ምንም ለሌላቸው ለችግረኞች በማሰብና እግዚአብሔር ስላደረገልን ልግሥና መልሰን በተግባር የምናመሰግንበት መሆን አለበት። (1ቆሮ. 16:2፤ ፊሊ4:14 - 20፤ ማቴ. 6:2 - 4፤ ማር. 12: 41 - 44፤ 2ቆሮ. 8: 1 - 15)



ለቅዱሳን ገንዘብ ስለማዋጣት
ለገላትያ አብያተ ክርስቲያናት እንደደነገግሁት
እናንተ ደግሞ አድርጉ።
እኔ ስመጣ ይህ የገንዘብ ማዋጣት
ያን ጊዜ እንዳይሆን ከእናንተ
እያንዳንዱ በየሳምንቱ በፊተኛው ቀን
እንደቀናው መጠን እያስቀረ በቤቱ
ያስቀምጥ። (1ቆሮ. 16: 1 - 2 )

## በመስጠት ባለአደራነት ቤተክርስቲያን ራሷን እንዴት መደገፍ ትችላለች?

በአሥራትና በመባ እንዲሁም በሥጦታ ከክርስቲያኖች የሚሰበሰበው ገንዘብ ቤተክርስቲያንን ራሷን ወደመቻል ደረጃ ያደርሳታል። ይህ ደግሞ ሁለት ውጤቶችን ያስከትላል:-

1. ቤተ ክርስቲያን ወንጌልን ለማድረስና ወደ ጌታ የመጡትን ደቀመዝሙር ለማድረግ ያስችላታል (በራስ መንገድ ወንጌልን ማዳረስ)
2. ቤተክርስቲያን ራሷን በራሷ ማስተዳደር ያስችላታል (ራስን ማስተዳደር)

ታላቁን ተልዕኮ ትዕዛዝ ለመወጣት (ማቴ. 28:18 – 20) የምትፈልግ ማንኛዋም ቤተክርስቲያን እንዲሁም በክርስቶስ እውነት ላይ የተመሠረተች ቤተክርስቲያን በተቻላት መጠን ራሷን ለመቻል ጥረት ማድረግ አለባት።

ምክንያቱም:-

(ሀ) _መጽሐፍ ቅዱሳዊ ዕቅድ ስለሆነ:-_ ወንጌልን የሚሰብኩና የሚያስተምሩ በውስጧ ያሉ የሙሉ ጊዜ አገልጋዮች በራስዋ በቤተክርስቲያኑቱ መደገፍ እንዳለባቸው ማመን አለባት። የእግዚአብሔር መልእክተኞች በውጭ እርዳታ መኖር



የለባቸውም። የቤተክርስቲያን ባለአደራነት ይህን ይጠይቃል። ቤተክርስቲያን ይህን ባታደርግ የእግዚአብሔር ሥራ ይቆማል።

> በዚያም ቤት ከእነርሱ ዘንድ ካለው
> እየበላችሁና እየጠጣችሁ ተቀመጡ
> ለሠራተኛ ደመወዙ ይገባዋልና (ሉቃስ 10:7)

(ለ) _ተገቢና ሥርአት የተከተለ እቅድ ስለሆነ:-_ አንድ የቤተ ክርስቲያን ወንጌላዊ ወይም መጋቢ (አገልጋይ) እንደቤተክርስቲያኒቱ ምእመናን የኑሮ ደረጃ አሥር ሰዎች በታማኝነት ሳያቋርጡ አሥራታቸውን ከሰጡ ሊደገፍ ይችላል። ይህ አነሥተኛ ገቢ ባላቸውም ምዕመናን ቤተክርስቲያን መካከልም ሊሆን ይችላል።

(ሐ) _በመንፈሳዊ ነገር ደህንነቱ የተጠበቀለት ማህበረ ምዕመን (ቤተክርስቲያን) ራሱን በራሱ የሚደግፍ መሆን ይናርበታል:-_ ገንዘባቸውንና ያላቸውን በታማኝነት ለቤተክርስቲያን የሚሰጡ ምዕመናን የሰጡት ገንዘብ ምን ላይ እንደዋለ ማወቅ ይፈልጋሉ። መስጠት በራሱ የባለቤትነትንና በሁሉ ነገር ለመሳተፍ ፍላጎትን ያስገኛል። ከውጭ በሚመጣ ገንዘብ ብቻ የሚታመኑና የሚደገፉ ቤተክርስቲያናት በእመዛኙ በትንሹ የሚረኩና ሌላ ተጨማሪ ሥራ ለመሥራት የመነሣሣት ባሕሪ የላቸውም።

(መ) _ያለምንም የሚሲዮን ድጋፍ የሚተዳደሩ የሙሉ ጊዜ አገልጋዮች የተሻለ አቋም አላቸው።_ ከውጭ ብዙ ድጋፍ የሚያገኝ አገልጋይ ከቤተክርስቲያን የሚያስፈልገው ድጋፍ አነስተኛ

ይሆናል። በአመዛኙ የሚሲዮን ድጋፍ የሚያገኙ አገልጋዮች ለቤተክርስቲያናቸው የሚሰጡት አገልግሎት ልግመት የተሞላበት ያደርጋቸዋል። ወይም አገልግሎቱ ትጋት በጣም አነስተኛ ይሆናል።

(ሠ) <u>ራስን በራስ መቻል ለእድገትና ለመስፋፋት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል።</u> ራስን በራስ መርዳት ዋነኛው ጥቅሙ ከማንኛውም ጥገኝነት ነፃ መሆንንና ራስን ወደ መቻል ደረጃ ያመጣል። ቤተክርስቲያን ያሏት ፕሮግራሞች እየተስፋፉ መሄዳቸው በዚያው መጠን ራሷን ልታስተዳድር ወደምትችልበት ደረጃ አልፋ ሌላውን ወደ መርዳት ደረጃ ትደርሳለች። ይህ እንቅስቃሴ ባጠቃላይ ለቤተክርስቲያን የመከናወን ስሜትና ለፕሮግራሞቿና ለተልዕኮዋ ተጨማሪ መስጠትን ያተርፍላታል።



## ሐ. <u>የቤተክርስቲያን ፈታኝ ሁኔታዎች</u>

ቤተክርስቲያን እንዳታድግና ተልዕኮዋን እንዳትወጣ አንዱ የሚፈታተናት ነገር ቢኖር ከውጭ (ከሚሲዮን ድርጅት) በሚመጣ ገንዘብ የመተማመንና የመደገፍ ነገር ነው። ጠንካራና የተሰጠች ቤተክርስቲያን ለመሆን በተቻላት መጠን ከዚህ የጥገኝነት ኑሮ በትግሏ መላቀቅ ይኖርባታል።

ይህ ሁኔታ በሚከተለው ታሪክ ሊመስል ይችላል። አንድ ወጣት አንድ ቀን ቢራቢሮ የዑደት ደረጃ ከአድገቷ ሂደት ውስጥ ካሉት ከሚባለው ደረጃ (ቀፎ መሳይ ሽፋን) ለመወጣት ስትታገል ይመለከታል። ካኩኑ ሲንቀሳቀስና ቢራቢሮዋ ያን በትግል ሰብራ ለመውጣት ስትታገል ያያል። ወጣቱ ቢራቢሮዋን ለመርዳት ያስባል። አንድ አነስተኛ ሴንጢ ከኪሱ ያወጣና አንዳንድ ቢራቢሮዋን የያዙ ክር መሳይ ነገሮች በመቁረጥ ትግሏን ለመቀነስና በቀላሉ ወጥታ እንድትበር ለማድረግ ሞከረ። ሆኖም ከዚያ ካኩን ከሚባለው ቀፎ መሳይ ከረጢት የወጣው ነገር ቢኖር ቅርጽ የለሽ ደካማና ምን እንደሆነ መለየት የማይችል ለጥቂት ደቂቃዎች ነፈስ ያለው ነገር ይመለከታል።

ወጣቱ ይህን በማድረግ በተፈጥሮ ቢራቢሮ ሆኖ መውጣት የሚችለውን የዕድገት ሕግን የሚቃረን ነገር ሠራ። እንዲሁ ቢተወውም መርዳት ባይሞክር ኖሮ ከብዙ ጥረት ትግልና ሥራ በኋላ በደንብ ቅርጽ ያለው በቀለማት የደመቀ ቢራቢሮ የተባለ ፍጥረት ከካኩኑ በወጣ ነበር። ይህ የሚያስተምረን ነገር ቢኖር በእንጨት

የተሠራ የጣራው ክዳን ጣራ የሆነ ግድግዳው የጭቃ ምርግ ያለው በአጥቢያ ቤተክርስቲያን ጉልበትና ገንዘብ በተሠራ ምዕመን የሞሉበት የአምልኮ ቤት በውጭ ገንዘብ በሸክላ በሲሚንቶና በቆርቆር ተሠርቶ ጥቂት ምዕመን ካሉበት የተሻለ መሆኑን ነው።

ራስን ለመቻል የሚደረግ ማንኛውም ጥረት በቤተክርስቲያን ምዕመናን ዘንድ መሰጠትን ያመጣል ይህም ደግሞ ራስን በራስ ወደመርዳትና መቻል ያሸጋግራል። ይህም በራሱ ለዕድገትና ለመስፋፋት የወንጌልን ተልዕኮ ለማድረስ ያመቻ ሁኔታን ይፈጥራል። ይህም እንደ.ገና የበለጠ ለሥራው ሰዎችን የተሰጡ ያደርጋቸዋል። ይህ ሁኔታ ታዲያ ቀጣይነት ያለው ይሆናል። ይህ የሚያመለክተን የዑደት ሕግን ነው። በዚሁ የዑደት ሂደት ውስጥ ራስን ለመቻል እንደ–ቦታ ላይ እንቅስቃሴው መጀመር ይኖርበታል። እንዴ እንቅስቃሴው ከተጀመረ ሂደ.ት በዑደት መልክ ይቀጥላል ለጤንነቱም እጅግ የሚረካና ቀጣይነት ያለው ይሆናል ማለት ነው። ትልቁ ጥያቄ ግን ራስን መቻል እንዴት ይቻላል? ምን ዓይነት እርምጃዎች መውሰድ አለባቸው? የቤተክርስቲያን መሪዎች በዚህ ሂደት ውስጥ ምን ድርሻ አላቸው?



# ክፍል ሦስት

## ራስን ለመርዳት (ለመቻል) የሚወሰዱ ተግባራዊ እርምጃዎች

### 1. ትክክለኛ መሠረት

ሰዎች ጌታን እንደግል አዳኛቸው ተቀብለው ክርስቲያን ሊሆኑና የደቀመዝሙር ትምህርት ሲሰጣቸው የባለአደራነት ትምህርትና መርህ አብሮ ሊሰጣቸውም ያስፈልጋል። ትምህርቱን ከተቀበሉና መርሁን ከተረዱ በሕይወታቸው ውስጥ የማይረሱትና ከክርስትና ሕይወት ልምምዳቸው እንደ አንዱ አካል አድርገው ይወስዱታል።

### 2. የባለአደራነት ትምህርት

በቤተክርስቲያን ውስጥ በሁሉም ዕድሜ ለሚገኙ ምዕመናን የባለአደራነት ትምህርት በአመት አንድ ጊዜ መስጠት ይኖረበታል። አባላት ራሳቸውን መጠየቅ ወደሚችሉበት ደረጃ ለመድረስ መማር አለባቸው። ራሳቸውን ሊጠይቋቸው የሚገቡ ጥያቄዎችም እኔ ማን ነኝ? ሃላፊነቴ ምድነው? ለማነውስ? ለቤተክርስቲያን ለምን እሰጣለሁ? ምን ያህል መስጠት አለብኝ? ለቤተክርስቲያን የሚገባኝ ገንዘቤን እንደፈለግሁ ባጠፋውስ?

ቤተክርስቲያን እነዚህንና ሌሎችን የተያያዙ ጥያቄዎችን አንስታ ከምዕመናን ጋር ብትወያይና ብታስተምር ለወንጌል አገልግሎት

መስፋፋት የጋራ ሃላፊነት ምዕመኑ ሁሉ እንዳለበት ለማስገንዘብ ያስችላል። በተጨማሪም ምዕመናኑ የባለአደራነትን ምንነት በውል ከተረዱ በክርስትና ሕይወታቸው እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ ያስተውላሉ።

<u>ማሳሰቢያ፡-</u> ይህ ዓይነቱ ግንዛቤ ሊገኝ የሚችለው ውል ያለው ቋሚ የሆነ የባለአደራነት የትምህርት ፕሮግራም በቤተክርስቲያኒቱ ውስጥ ተመሥርቶ የሚሰጥ ከሆነ ብቻ ነው።

ለዚህ አገልግሎት ሊውል የሚችል እጅግ በጣም ጥሩ ስለ መስጠት የሚያስጠና የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት የያዘ መጽሐፍ ለአፍሪካ ቤተክርስቲያናት የሚሆን ስላለ አድራሻውን በዚህ መጽሐፍ መጨረሻ ገጽ ላይ ያገኛሉ።

2. <u>መሪዎች መስጠት አለባቸው፡-</u> እንደሚከተለው አባባል ከሆነ መሪዎች መስጠት ይኖርባቸዋል። አባባሉም "ሰዎች ምሳሌ ከሚሆኑላቸው ሌሎች ሰዎች ይማራሉ።" ምክንያቱም የቤተክርስቲያን መሪዎች በመስጠት ቀዳሚ በመሆን ለምዕመኑ ምሳሌ መሆን ይጠበቅባቸዋል። አሰጣጣቸውም ቋሚነት ያለው ሆኖ ታማኝነት ያለበት መሆን ይኖርበታል። በኢትዮጵያ አንድ አባባል አለ። ይኸውም "ንጉሡ አጎንብሶ ከሄደ ሕዝቡ እንዲሁ አጎንብሶ መሄድ ይጀምራል።" የቤተክርስቲያን መሪዎች በምዕመኑ ዘንድ የተከበሩና



ተመልካች ያላቸው ናቸው። ስለሆነም እነሱ ምሳሌ መሆን አለባቸው። ምዕመኑም የነሱን ፈለግ ተከትሎ ያየውን ያደርጋል። ምዕመናን ታማኝ ሊሆኑ የሚችሉት መሪዎቻቸው ታማኝ ሲሆኑላቸው ነው።

3. <u>የገንዘብ ተጠያቂነት አስፈላጊ ነው፡-</u>

በአጥቢያ ቤተክርስቲያንና በዋናው ጽ/ቤት ሆነ የቤተክርስቲያን ነክ የሥራ ዘርፎች ሁሉ ወቅታዊ የገንዘብ ሪፖርት ለመዕመናንና ለሚመለከታቸው ማቀረብ ተገቢ ነው። ይኸውም ምን ያህል እንደተገኘ ምን ያህሉ በሥራ ላይ እንደዋለ ምዕመኑ የማወቅ መብት አለው። ይህ እርምጃ ግልጸኝነትንና ታአማኒነትን ያጎለብታል። ምዕመናን በፕሮግራም ዕቅዳቸው የት እንዳሉ አጉልቶ ያሳያል። ብዙ ጊዜ ይህ ልምምድ እየጎለበተ በሄደ መጠን ምዕመናን የመስጠት ልማዳቸው ከፍ እያለ ይሄዳል። ይህ ሪፖርት የማድረግ ልምድ በተጨማሪ በቤተክርስቲያኒቱ ውስጥ በምዕመኑ ዘንድ የባለቤትነት ስሜት እንዲያድርባቸው ያደርጋል። ምን ጊዜም ቢሆን የተሰበሰበው ገንዘብ በዕቅድ ለተያዘለት የቤተክርስቲያኒቱ ሥራ ብቻ መዋል ይኖርበታል።

# ከራስ አለመቻል ወደመቻል

በክፍል ሁለት ወደ ራስ መቻል የሚያደርሰንን አንዳንድ መወሰድ ስለሚገባቸው የእርምጃዎች ጉዞ ተመልክተናል። እነዚህ ለቤተክርስቲያን ዕድገት በጣም ጠቃሚ እርምጃዎች ናቸው። ሆኖም ጉዞው በዚህ ብቻ አያበቃም። በእርምጃዎቹ ሦሥተኛው ደረጃ ጤናማነት የሚያለብስ እርምጃ ነው። እስቲ ሦሥተኛውን እርምጃ ለመረዳት ሁለቱን የመጀመሪያ የተመለከትናቸውን እንደገና እንመልከታቸው።

## 1. <u>ራስን አለመቻል/ጥገኝነት:-</u>

ራስን አለመቻል /ጥገኝነት ማለት የቤተክርስቲያኒቱ ገንዘብ በሙሉ ወይም አብዛኛውን እጅ ከውጭ ሲመጣላት ነው። እንደዚህ አይነቷ ቤተክርስቲያን ከፍተኛ የሆነ ገንዘብ ከውጪ ካላገኘች በስተቀር ሕልውናዋ እየተዳከመ ይሄዳል። ኑሮዋ የትግል ኑሮ ይሆንባታል። ከዚህ የተነሳ በራሷ ውሳኔ ለመተዳደር አትችልም። ገንዘቡን የሚሰጠው ድርጅት በምታደርገው ነገር ሁሉ ጣልቃ ስለሚገባባት በመንፈሳዊ አገልግሎት ዘርፎች ለማደግ ትቸገራለች። በመሪዎቿም መካከል በአንድነት ለማገልገል ችግር ይገጥማታል። ባጠቃላይ በምዕመኑ ዘንድ ለቤተክርስቲያን ራሳቸውን ለመስጠት ያለው ትግል ከፍተኛ ይሆናል። በመንፈሳዊነትም ሆነ በወንጌል ስርጭት ዕድገትም አይኖርም።

ጥገኝነት (ራስን አለመቻል) ሌላም የማያስደስት ውጤት አለው። ቤተክርስቲያኒቱ የመከናወን ስሜትን ይነፍጋታል።



በውጭ ድጋፍ ከመኖር የተነሣ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ አመስጋኝ ከመሆን ይልቅ በገንዘብ ለጋሾችዋ ላይ የቅሬታ ስሜት ያድርባታል (ገንዘብ ባይሰጡን ኖሮ ተፍጨርጭረን ራሳችንን በቻልን ነገር። አበላሽተውናል ወደማለቱ ትደርሳለች።) ከዚህ የተነሣ ራስዋን ለመደገፍ ባለመቻልዋ የለማኝነት ስሜቷ ያስፈራታል። በዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ያለች ቤተክርስቲያን በቶሎ ራሷን ከሁኔታው ማላቀቅና መውጣት ይኖርባታል።

## 2. <u>ራስን መቻል:-</u>

ቤተክርስቲያን ራሷን በራሷ የመደገፍና ራሷን ወደመቻል ደረጃ ከደረሰች ለምዕመኗ ሁል ጊዜ በዕቅድና በፕሮግራም የባለአደራነትን ትምህርት ማስተማር አለባት። ይህን ብታደርግ ምዕመኗ ከፍተኛ የሆነ ለቤተክርስቲያናቸው የተሰጠ ሕይወት ይኖራቸዋል። ቤተክርስቲያኒቱ ከዚህ የተነሳ በራሷ ምዕመን ራሷን ለማስተዳደር በራሷ አገልግሎቷን አድማስ ለማስፋት በማንኛውም ረገድ ራሷን ለመደገፍ ትችላለች ማለት ነው።

## <u>እርስ በእርስ መደጋገፍ:-</u>

ይህ ሦሥተኛውና የመጨረሻው ደረጃ ነው ይህም ራስን ከመቻል ወዶ. ሌላ ቤተክርስቲያን ወደ መደገፍና ጎን ለጎን አብሮ ለመስራት የሚያስችል ደረጃ የሚያደርስ ነው። በዚህም ብዙ በረከት ይገኛል።

## እርስ በእርስ መደጋገፍ ማለት ምን ማለት ነው?

እርስ በእርስ መደጋገፍ ማለት አንድ ግለሰብ ወይም ድርጅት ራሱን በራሱ መደገፍ የሚችል ሆኖ ከሌሎች ሰዎች ወይም ድርጅቶች ጋር ጎን ለጎን አብሮ በመረዳዳት መሥራት ማለት ነው። በሌላ አገላለጽ ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ 1:11፲ 12 እንደሚገልጸው "ብመካከላችን ባለች በእናንተና በእኔ እምነት አበረን በእናንተ እንድንጽናና ነው ማለት ነው። ይህ በእኩልነት ደረጃ ሁለቱም ወገኖች ያላቸውን አንድ ላይ በማድረግ አብሮ ለመሥራት መዘጋጀትን ያሳያል። ይህ በአንድ ቃል በእንግሊዘኛ ፓርትነርሽፕ (Partnership) ይባላል። ምናልባት ቃሉ ቀላል ወይም ተራ ይሆናል እንጂ "ሽርክና " ልንለው እንችላለን።

የአብያተክርስቲያናት ዓላማም ይህ ሊሆን ይገባዋል። ሁሉም ራሳቸውን በገንዘብ መርዳት ከቻሉ እርስ በእርሳቸው ወደዚህ "ሽርክና " እርስ በእርስ በመደጋገፍ በጋራ ለመስራት መቻል ይኖርባቸዋል። በጋራ የወንጌል ተልዕኮ፣ በጋራ የሥነመለኮት ትምህርት ቤት መክፈት እንዲሁም በውጪ ካለ መንፈሳዊ ቤተ ክርስቲያን ወይም ድርጅትም ጋር ተመሳሳይ ሽርክና ውስጥ መግባት ይችላሉ ማለት ነው። ይህ ታድያ መንፈሳዊ አቋማቸው ጤናማና ስምም መሆኑ በትድሚያ መጣራት ይኖርበታል።



ቤተክርስቲያን ወደዚህ ደረጃ መድረስ ከቻለች ስኬታማ የሆነ ውጤት ይኖራታል። ለእግዚአብሔርም የመሰጠቷ ነገር እያደገ ይሄዳል። ከወቀሳ ነፃ በሆነ መልኩ ከሌሎች ጋር ተመሳሳይ ራዕይ ካላቸው ቤተክርስቲያናት ወይም መንፈሳዊ ድርጅቶች ከሀገርም ሆነ ከውጭ አብራ ብትሠራ የታላቁን ተልዕኮ አገልግሎት መወጣት ትችላለች። የተጠራችውም በምድር ያለችውም ለዚህ ነውና።

<u>ክፍል አራት</u>

# ቤተክርስቲያን ከፍ ወደአለ የባለአደራነት ብስለት ደረጃ ለመድረስ መጠየቅ የሚገባት ጥያቄዎች

በዚህ መጽሐፍ መግቢያ ላይ ለዕድገትና ለብስለት ደረጃ የሚያበቁ ሦሥት ነጥቦች ተጠቅሰው ነበር። የበለጠ በምዕመናን ዘንድ የታወቁ ለማድረግ የቤተክርስቲያን መሪዎች እንዳመቹነቱ ለየት ያለ ቦታና ጊዜ ፈልገው ከዚህ በታች ያሉትን ጥያቄዎች ለውይይት ማቅረብ ይችላሉ። በዚህ በአንድ ላይ በሚሆኑበት ጊዜ ምዕመናን ቤተክርስቲያናቸውን ከራስን አለመቻል ወደ መቻል ብሎም ወደ ሌላውን መደገፍ (በሽርክና መስራት) ደረጃ ማሸጋገር እንደሚችሉ መማር ይችላሉ።

## ሀ. <u>ባለአደራነት</u>

1. ስለባለአደራነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ አመለካከት አላቸው ወይ? ምን ያህል የተረዱ ናቸው? እንዴት እናስተምራቸው?
2. በምዕመናን ዘንድ ስለዚህ ጉዳይ ምን ዓይነት ለውጥ እንዲመጣ እንፈልጋለን? በቋሚነት ስለባለአደራነት የማስተማረ ነገርስ አስፈላጊነት?
3. ምዕመን አሁን ካሉበት ስለባለአደራነት የመረዳትደረጃ ወደ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አመለካከት ይዞት ወደሰው ባለአደራነት ለማሸጋገር ምን እርምጃዎች መውሰድ አለብን? የተሰጡ ሰዎች እንዴት እናደርጋቸዋለን?

## ለ. <u>ብስለት የተላበሰ ክርስቲያናዊ አመራር በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና እውቀት ያደገ</u> (2ጴጥሮስ 3፤18)

1. ብስለት የተላበሰ ክርስቲያናዊ አመራር በአጥቢያ ቤተክርስቲያናት ደረጃ ለማሳደግ አሁን ምን እያደረግን ነው? (የቤተክርስቲያን መሪዎች እድገት ምን ደረጃ ላይ ይገኛል?)
2. በቤተክርስቲያን (አጥቢያ) መሪዎች ዘንድ ምን ዓይነት ዕድገትና ለውጥ ማየት እንፈልጋለን? ብስለት ያላቸውና ሃላፊነትን መቀበል የሚችሉ መሪዎች እንዴት ሊኖሩን ይችላሉ?
3. እንዲህ ዓይነት መሪዎች ለማፍራት ምን እርምጃ መውሰድ አለበት ?

ሐ. <u>ተጠያቂነት፡-</u>

<u>ሁሉ ነገር በአግባብና በሥርዓት ይሁን (1ቆሮ.14፤40)</u>

1. በቤተክርስቲያናችን ውስጥ ያለው የገንዘብ አያያዝ ምን ይመስላል? ለምዕመኑ ወቅታዊ ሪፖርት እንሰጣለን ወይ?
2. በገንዘብ በኩል ራስን ለመቻል ወደሚያስችል ደረጃ ለመምጣት በቤተክርስቲያናችን ምን ለውጥ ማየት አለብን? ምዕመናን በሙሉ ልባቸው እኛን መሪዎች በገንዘባቸው ምን ብናደርግ ሊተማመኑብን ይችላሉ?
3. ከ '1' ወደ '2' ነጥብ ለመሸጋገር ምን እርምጃ መውሰድ ይኖርብናል?



<u>ማጠቃለያ፡-</u>

እያንዳንዱ ቤተክርስቲያን የባለአደራነትን፣ የተጠያቂነትንና የመሪዎች አዘገጃጀት አሠራርን ምን መሆን እንዳለበት መወሰን አለበት፡፡ ከዚህ በታች መሠረተ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ከላይ የተመለከቱትን ስለ ሦስቱ አሠራሮች የተለማመደችውን ባጭሩ ቀርቧል፡፡

## <u>ክፍል አምስት</u>

### መሠረተ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን - እንዴት ራሷን ለመቻል በቃች?

ከ1969 ዓ.ም. ጀምሮ የገንዘብ ችግር እንደሚኖር የቤተክርስቲያን መሪዎች ተረዱ፡፡ ዋናው ምክንያቶች፡- አንደኛ አብዛኛውን ገንዘብ ከውጭ የሚስዮን ድርጅት ይመጣ ስለነበረ ሁለተኛ - ምዕመኑ የሚሰጠው አነስተኛ በመሆኑና እንዲሁም ከ1940 ዓ.ም. ጀምሮ ከመሠረተ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን የጀመረው የሚስዮን ድርጅት ሙሉ በሙሉ ባይረዳም ቀስ በቀስ ዕርዳታውን እየቀነሰ ቢመጣም ይህን ሊሸፍን የሚችል ከሀገር ውስጥ ከምዕመናን የሚገኝ ገንዘብ አልነበረም፡፡ የነበረው የኮሚኒስት ሥርአትም ሚስዮናውያንን ለማባረር ይዝት ስለነበር የሚገኘውም እርዳታ ሊቆም እንደሚችል የቤተክርስቲያን መሪዎች ግምት ውስጥ አስገብተውት ነበር፡፡

ይህን ችግር ለመፍታት ብዙ ሀሳቦች ተሰንዝረው ነበር። በመጨረሻም የተገኘውና የተወሰደው አማራጭ የቤተክርስቲያን አባላትን ከመጽሐፍ ቅዱስ ስለ አሥራት ማስተማር ነበር። ይህ ትምህርት ከዚያን ጊዜ ጀምሮ መስጠት ቀጠለ። አዳዲስ አባላትም በደቀመዝሙርነት ሥልጠና ወቅት ለቤተክርስቲያን ስለመስጠት እንዲማሩ ተደረገ።

ይህ እርምጃ እንዲሁም በመሪዎች ዘንድ የታየው መልካም ግልጽነት፣ ተጠያቂነት፣ ታማኝነትና በመስጠት ምሳሌነት ምዕመኑን በማበረታታቱ ዛሬ ቤተክርስቲያኒቱ ራሷን በገንዘብ ለመደገፍና የታላቁን ተልዕኮ ሥራ ዘጠና አምስት በመቶ ለማካሄድ ችላለች።

## ተጠያቂነት:- በአጥቢያ ቤተክርስቲያናት ውስጥ

መሠረተ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ይህን እንዴት ታካሂዳለች (ታስተናግዳለች)? እያንዳንዱ አጥቢያ ቤተክርስቲያን በሽማግሌዎች ይመራል። በደበልጥ የሚያገለግሉ መጋቢዎች ወይንም ወንጌላውያን ይኖሩታል። ሽማግሌዎች የሚመረጡት በመጽሐፍ ቅዱስ በተሰጠው መሥፈርት መሠረት ነው። (1ጢሞ. 3:1 - 7፤ ቲቶ 1:6 - 9) እነዚህ ሽማግሌዎችና የሙሉ ጊዜ አገልጋዮች በአንድ ላይ የየዓመቱን በጀት ያዘጋጃሉ። ምዕመናን ለቤተክርስቲያኒቱ አሥራት ወይም ሥጦታ በሚሰጡበት ጊዜ ደረሰኝ ከቤተክርስቲያኒቱ ይሰጣቸዋል። የተሰበሰበው ገንዘብ በአቅራቢያ ባንክ ካለ በባንክ ይቀመጣል። በባንክ ያለ ሒሳብ ሁሉ በሁለት ወይም በሦስት ፈራሚዎች ይንቀሳቀሳል። በየዓመቱ



መጨረሻ ላይ ሽማግሌዎቹ ለምዕመናኑ የሂሣብ ሪፖርት ይሰጣሉ። ይኸውም የተያዘው በጀት በዓመቱ የገባው ገቢ የወጣውን ወጪ ሪፖርት ያደርጋሉ።

ይህ አሠራር በምዕመኑና በሽማግሌዎች መካከል መተማመንንና ግልጽነትን አትርፏል። ሽማግሌዎች በምዕመናን ዘንድ ተጠያቂነት ስላለባቸው አሠራራቸውን ግልጽ ማድረጋቸው የሚጠበቅባቸው ሃላፊነት እንደሆነና ወደፊት በሚመረጡ ምዕመናንም የታወቀ ይሆናል። በቅርቡ የሂሣብ ምርመራ (ኦዲት) ማድረግ ተጀምሯል። ይህም ልምድ ወደ አጥቢያዎችም ወደፊት ይሸጋገራል።

## መሠረተ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን መሪዎችን እንዴት ታሰለጥናለች?

በመሠረተ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን የሥልጠና ዓላማ የተመሠረተው በ2ኛ ጢሞ. 2:2 ፍሬ ሃሳብ ላይ ነው። “ብዙ ሰዎች የመሰከሩለትን ከእኔም የሰማኸውን ሌሎችን ደግሞ ሊያስተምሩ ለሚችሉ ለታመኑ ሰዎች አደራ ስጥ”።

ይህን ተግባራዊ ለማድረግ መሠረተ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን መሪዎች ለማሰልጠን ሦሥት ስልቶችን ነድፋለች።

1. የመጀመሪያው ሥልት የሚባለው <u>የአንድ ዓመት ለክርስቶስ</u> አገልጋዮች ሥልጠና ነው። ባለፉት 20 ዓመታት ይህ ሥልጠና ወጣቶችን ከክርስቶስ ጋር የጠበቀ

አፍሪካ የሚገኙ የቤተክርስቲያን መሪዎችን፣ ሽማግሌዎችን፣ወንጌላ ውያንና የቤተክርስቲያን አጋዥ ድርጅት መሪዎችን ለመቀስቀስና በራሳቸው ተጨማሪ ጥናት አድርገው የተሻሉ ባለአደራዎች የሚሆኑ በትን መንገድ እንዲፈልጉ ነው ። መጽሐፉ ዓይን ከፋችነት ሚና ይኖራታል ብሎ ጸሐፊው ያምናል ።

በክፍል አራት በዚህች መጽሐፍ ውስጥ ተከታታይ ጥያቄዎች ተሰጥተዋል ። በተቀመጡበት ቅደም ተከተል መሪዎች ቢወያዩባቸው ጠቃሚነታቸው እጅግ ከፍተኛ እንደሚሆን አልጠራጠርም ። ተፈላጊ ውን የቤተክርስቲያን ዓላማ ያስጨብጣሉ ብዬ አስባለሁ ።

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የሰፈሩት ነጥቦች ለስብከትና ለትምህርት መርጃዎች ሆነውም ሊያገለግሉ ይችላሉ ።

ከዚህ ጋር በማያያዝ ባለአደራነትን በተመለከተ ለቤተክርስቲየን ስለመሥጠት ለመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚረዳና ጠቃሚ የሆነውን "*ክርስቲያን ጊቪንግ*" (Christian Giving) በሬቨራንድ ዳንኤል አጉሶ አቢሮ የተጻፈውን ያንብቡ ። መጽሐፉ የታተመው በO.A.I.C/T.E.E ሲሆን የሚገኘውም በሚከተለው አድራሻ ነው ፡

የፖ.ሳ.ቁ 21736 ናይሮቢ፣ ኬንያ ነው

የእግዚአብሔር ታማኝ ባለአደራ በመሆን ቤተክርስቲያንዎን ወ ይም የቤተክርስቲያን አጋዥ ድርጅትዎን ለብስለት ደረጃ ለማብቃት ጌታ ይርዳዎት፣ ይባርክዎት ።



## Works Consulted


**Fairchild, James G.T. <u>All That We Are We Give</u>, Herald press Scottsdale, 1977.**

**Fromke, De vern <u>No Other Foundation</u>, Cloverdale, IN. 1965.**

**Hodges, L. Melvin. <u>The Indigenous Church</u>, Gospel Publishing House, Springfield. 1976.**

**Kauffman, David. <u>Managers With God</u>, Herald press Scottdale, 1992.**

**<u>The Challenges of Christian Stewardship</u>, Herald Press Scottdale, 1955.**

**Mehoney, Ralph. <u>The shepherds Staff</u>, World Map, san Fernando. 1993.**

**Martin, Alfred. <u>Not My Own</u>, moody press, Chicago.**


♦